# ልዩ-ልዩ ግጥሞች

ሰው መምሰል ቀላል ነው፣ እምብዛም አይከብድም
ከልብ ካለቀሱ ዕምባም አያገድድም!
ግን ዝንጀሮ ሞልቷል ሰው እየመሰለ
የካንገት በላይም፣ የውሸት ለቅሶ አለ…

* * *

ነጭ ወረቀት አለ፣ ጥቁርም አይጠፋም
አንድ-አንድ ቁም ነገር መጫሩ አይከፋም
ነጩ ላይ በጥቁር፣ በጥቁሩም ነጭ
በጨለማው ብርሃን ማብራት፣ ማብለጭለጭ!

* * *

ቢሄዱት፣ ቢሄዱት መች ያልቃል መንገዱ
ቢስቡት፣ ቢስቡት ረዥምም ነው ገመዱ
ስንመለከተው ቆም ብለን ከዳሩ
ሕይወት ዘመቻ ነው፣ ጉዞውና አዳሩ…

* * *

መከራን መቻል
ድል ያመቻቻል
እንጀራንም መጣል
ችጋር ያመጣል

* * *

"ተዋት! ተዋት!" አሉኝ፣ ልተዋት አልወድም፣
"ትቅር! ትቅር!" አሉኝ፣ መቅረትዋን አልወድም፣
የጎሪጥ ዓይን አይታኝ ስትሄድ ግድም፣ አግድም
ብሞት አልለቃትም ብትወድም ባትወድም…

* * *

መውደቅ መነሳትም ያለ ነው በዓለም
እንደ ቆመ እሚኖር ማንም ሰው የለም፣
ግን ያወዳደቅም አለው እንጅ ዓይነት
ከአልጋ መውደቅ አለ፣ ደግሞም ከዓለት
ወድቆ፣ ተሰባብሮ፣ ከመንኰታኰት!
ተንከባልሎ ወርዶ መስመጥ ከዓዘቅት
እግዚሄር ያውጣን ከሁሉ መዓት…

ገ/ኢ. ጐርፉ።